# ኢትዮጵያችን

*የአንድ ሀገር! አንድ ሕዝብ! ኢትዮጵያችን ሕዝባዊ ንቅናቄ (አሀ! አሕ! ኢሕን) ልሳን*

ኢትዮጵያችን ቅጽ 1 ቁጥር 3 ህዳር ፫ ቀን ፪ ሺህ ፱ ዓ.ም.

## ዳግማዊ ጉልቻ

በየካቲቱ 1966 ዓ.ም. በኢትዮጵያ ሀገራችን የተቀጣጠለው ሕዝባዊ አመጽ፤ በጊዜው የነበረውን የዓፄ ኃይለሥላሴ መንግስት መቆሚያ መቀመጫ ባሳጣበት ጊዜ በጸሐፊ ትዕዛዝ አክሊሉ ሀብተወልድ የሚመራው የሚንስትሮች ካቢኔ እራሱን ከስልጣን አገለለ። ንጉሡ ከገቡበት አጣብቂኝ እፎይታ ለማግኘት፣ ከጭንቀት ብዛት ልጅ እንዳልካቸው መኮንንን ጠቅላይ ሚኒስቴር አድርገውና መሰሎቻቸውን በሚንስቴርነት በመሾም "ፋታ ስጡን" ድምጻቸውን አሰሙ። የየካቲት አብዮት በንጉሡ አገዛዝ ላይ ያነጣጠረ ሕዝባዊ አብዮት ስለነበር የሕዝቡ ፈጣን ምላሽ "ጉልቻ ቢቀያየር ወጥ አያጣፍጥም" ነበር። ሕዝብ በመንግሥት ካመረረ የሚተካውን መተንበይ ባይችል እንኳ የጠላውና ዳር እስከዳር የተነሳበት አገዛዝ ካልተወገደ እርካታ የለውምና የዓፄው መንግስት እንዳበቃለት ቆርጦ መነሳቱን ትግሉ በየአቅጣጫው ማቆሚያ ባጣ ማዕበል ተቀጣጠለ። በዓፄው ሥርዓት መውደቅ እርካታውን ያገኘው ሕዝብ ሳይውል ሳያድር ትግሉን መቀማቱን፣ ፍላጐቱ አቅጣጫውን መሳቱን ቢገነዘብም አሁንም ለመብቱና ለነፃነቱ ትግሉን ቀጠለ።

"ዳግማዊ ጉልቻ" እንዲሉ የህወሀት/ኢሕአዴግ የሰሞኑ የጭንቅ ትርዕይት ጠቅላይ ሚኒስቴር ኃይለማርያምና አዲሱ አሿሿማቸው ነው። "አስተዳደራዊ ብልሹነት" አለብን በሚል ማዘናጊያ የተጀመረው ወያኔያዊ ትርዕይት የኢትዮጵያ ሕዝብ ዶክተርና ፕሮፌሰር መባል የቁስሉና የብሶቱ የፈውስ መርፌ ይመስል ተሾሞለታል። ወያኔ/ኢሕአዴግ የመጨረሻ የእስትንፋስ ጣሩን ለማራዘም ሕዝቡን ለማዘናጋት የማይፈነቅለው ቅጥፈት አይኖርም። አያልቅበት ወያኔ ዛሬላይስ ውሸቱም፣ ማጭበርበሩም ሸሽቶታል።

የኢትዮጵያ ሕዝብ ጥያቄ ወያኔ በቃን ነው። ወያኔ አፋኝና ገዳይ ሥርዓት መሆኑን በልጆቼ አይቸዋለሁና የደም ግብሬ ይብቃ ነው። ወያኔ ዘራፊና አፈናቃይ ሥርዓት መሆኑን ተፈናቅዬ የላስቲክ ጎጆ መታቀፌ ያብቃ ነው። ወያኔ ሴሰኛና ጋጠ ወጥ አገዛዝ ለመሆኑ በሴት ልጆቼ ላይ ለሚደርሰው ግፍና በደል አስረጅ አልፈልግምና በቃኝ ወያኔ ብሏል። ወያኔ ዘረኛና ከፋፋይ አገዛዝ መሆኑን ለዘመናት ችግራችን ፍቅር ከሆኑ አንድ እናት ልጆች እንድንናከስ ማድረጉ ማብቃት አለበት ነው። ለመብቴ፣ ለሀገር አንድነት፣ ለዕለት ኑሬዬ ድምጽ ያሰሙ፣ ብዕራቸውን ያነሱ ወደ እስርና ስቃይ ከታች ሥርዓት ያብቃ ነው ጥያቄው። ከማንም በላይ 25 ዓመት በገጠሩ አርሶ አደር ዘንድ፣ በከተማው ነዋሪ ዘንድ፣ በተማሪው ሕይወት፣ በላብ አደሩና በመንግሥት ሠራተኞች፣ በሴቶች እህቶቻችንና በሕፃናት፣ በአዛውንት እናቶችና

አባቶች ስቃይ፣ በሃይማኖቱ፣ በባህሉ፣ በማንነቱ የዘመተበትን የግፍ አገዛዝ በቃ ያለ ሕዝብ በወያኔ የፌዝ ሹም ሽረት እንደማይዘናጋና ወያኔ በሚገባው ቋንቋ እንደሚነገረው ጊዜው እሩቅ አይሆንም። ወያኔ የማሾፍ ዕድሉን ከበላው ቆይቷል። በህወሀት/ኢሕአዴግ አገዛዝ ላይ በየአቅጣጫው የተንቀሳቀሰው ሕዝባዊ እምቢተኝነት በሥርዓቱ መወገድ ብቻ ሳይሆን መውደም እንደሚደመደም በእርግጠኝነት መናገር ትንቢት አይደለም። የሕዝብ ኃይል ለጠላቱ እሳተጎሞራ ነውና። የሕዝብ ኃይል ለወያኔ ደራሽ ውኃ ነውና። የሕዝብ ኃይል ለኢሕአዴግ ኢልኖይ/መብረቅ ነውና። የሕዝብ ኃይል ወያኔን ይውጣልና።

በግምባር ቀደም መሪ ወያኔዎቹ ስብሐት ነጋ፣ በረከት ስምዖን፣ ስዩም መስፍን፣ ሳሞራ፣ አዜብ መስፍን ወዘተ እና ለሂደታቸው ቀዳሚ ተሳታፊዎች ሕላዊ ዮሴፍ፣ አዲሱ ለገሠ፣ ተፈራ ዋሉዋ፣ አባ ዱላ ገመዳ መሰል ሀገርና ሕዝብ በታኞች መጋረጃ በስተጀርባ የሚሠራውን ደባ  ጠንቅቆ የሚያውቀው የኢትዮጵያ ሕዝብ በዶክተርና ፕሮፌሰር ጋጋታ ዕልል ይልልኛል ብሎ መጠበቅ በሕዝብ ቁስል ላይ እንጨት ሳይሆን ጦር መስደድ ነው። የወያኔን አምስት ለአንድ ጥርነፋ በጥሶ አደባባይ የወጣ ሕዝብ፣ የወያኔን ባንዲራ አውርዶ የኢትዮጵያ ሰንደቅ ዓላማ ያውለበለበ ጀግና ሕዝብ፣ የወያኔን ዘረኝነት በጥሶ ኦሮሞው ለአማራው፣ አማራው ለኦሮሞው ደም የከፈሉበት ሰልፍ፤ የወያኔን/ኢሕአዴግን ገዳይ አስቸኳይ ጊዜ አዋጅ የወያኔ መቀበሪያ ማድረጉ አይቀሬ ነው።

ህወሀት/ኢህአዴግ የኢትዮጵያን ሕዝብ አንገብጋቢ ጥያቄ ምንድ ነዉ? ብሎ በመረዳት እራሱን ሽሮ ሀገር ለሕዝብ ከማስረከብ ይልቅ፤ እርስ በርሱ "የሹም ሽረት ለውጥ" አድርጓል። ግና የኢትዮጵያ ህዝብ የተደበደበው፣ የተረገጠው፣ የተገደለው፣ በየዱሩ የተጣለው፣ ከሀገር ሀገር  የተሰደደው፣ ግርማይን በሃጎስ ለመቀየር ሳይሆን፤ ወያኔን በሕዝብ ተመራጮች ለመቀየር ነው። ሕዝባችን የሚታገለው ለፍትህ፣ ለእኩልነትና ለአንድነቱ ባጠቃላይ ለመሰረታዊ የሥርዓት ለውጥ ነው።

ይህንንም ለውጥ የሚያመጣው ያለው ግፈኛ መንግስት ወይንም በውጭው ዓለም ያሉት ፖለቲከኞች ሳንሆኑ፤ ራሱ ለመብቱ የሚታገለው ሕዝብ ብቻ ነው። የሚጠቅመውንና የሚጎዳውን፤ ለሕዝብ ጥቅም ወይስ ለግል ጥቅም የሚቆመውን ለይቶ የሚያውቅለት ማንም ባዕድ ሳይሆን እራሱ ነው። ሕዝባችን ድሉን የሚጎናጸፈው በትግሉ ብቻ መሆኑንም ጠንቅቆ ያውቃል።

ህወሀት/ኢህአዴግ በየጊዜው የረሸናቸው በብዙ ሺህ የሚቆጠሩ ወጣትና አዛውንቶች የታገሉለትን ስር ነቀል የሥርዓት ለውጥ ለማቀዝቀዝና ለማደናገር የስልጣን ሹም ሽርና ጋጋታ የተለመደ ሹፈት ጭራሽ ለሕዝብ ያለውን ንቀት አመላካች መሆኑን በመገንዘብ ትግሉን በማፋፋም ወደ ዳር ማድረስ ይጠበቅብናል።

"ፍየል ወዲህ ቅዝምዝም ወዲያ" እንዲሉ በሕዝብ ጥያቄ የማሾፍና የማላገጥ እብሪት የወያኔና አምባገነኖች መጨረሻ ነውና ሕዝባዊው እምቢተኝነት በወያኔ/ኢሕአዴግ መገርሰስ እንዲጠናቀቅ «አንድ ሀገር! አንድ ሕዝብ! ኢትዮጵያችን ሕዝባዊ ንቅናቄ» የተደራጀና

የተቀናጀ ሕዝባዊ ድል፤ ብስራት ሊኢትዮጵያችን ይሆን ዘንድ አስፈላጊውን መስዋዕትነት ለመክፈል ከሕዝባችን ጐን ተሰልፈናል።

ወያኔ/ህወሀት ሥልጣን ይዞ 11 ዓመት ሀገርና ሕዝብ አፈር ድሜ ካስገባ በኋላ በውስጡ መፈረካከስ ሲገጥመውና ሲንገታገት "በስብሰናል፣ ተጨማልቀናል" ብሎ በሕዝብ ፊት በሠራው ማላገጥ እንዴት አድርጎ ወቅቱን ሊያልፍ እንደአስቻለው የሚዘነጋ አይደለም።

በቀጣይነት በ1997 ዓ.ም. ምርጫ "ራዕይ የሌለው ተቃዋሚ እስቲ ይግጠመን" እያለ ሲያሾፍ የሕዝብ ማዕበል በምርጫ ካርድ ከጨዋታ ሊያሶጣው ሲል "ጣት ቆራጩን" የአስቸኳይ ጊዜ አዋጅ አውጆና የወታደሩን ዕዝ በሙሉ በቁጥጥሩ ሥር አድርጎ የሾለከው የመለስ ዜናዊ አገዛዝ ዛሬም በኃይለማርያም ደሳለኝ አፍ የተለመደውን ፈሊጥ ሲያላዝን ይስተዋላል።

"በመልካም አስተዳደር እጦት ተበሳብሰናል" የሚለው የጠቅላይ ሚንስቴር ኃይለማርያም ደሳለኝ አስተዳደር ለመፍትሄው የአስችኳይ ጊዜ ሀገርና ሕዝብ ገዳይ አዋጅ አውጆ እያቅራራ ይገኛል። ይህ አዋጅ ከወጣበት ጊዜ አንስቶ በርካታ የሀገሪቷ ልጆች በየጊዜው ወደ እስር እየተጋዙ ነው። ደብዛቸው የሚጠፋና የሚገደሉ በርካታዎች ናቸው። በሀገራችን የተጀመረውን ፀረ-ወያኔ ሕዝባዊ እንቅስቃሴ ለማኮላሸትና አንገት አስደፍቶ ለመግዛት ህወሀት/ኢህአዴግ በማንኛውም የሀገሪቷ አካባቢ የአገዛዙ ካድሬዎችና ጀሌዎች የፈለጉትን ቤት የመፈተሽ፣ የመበርበር፣ የመዝረፍ መብት ተሰጥቶአቸው እየተንቀሳቀሱ ይገኛሉ። ማሰር፣ ቋንቋ ሊገልጸው ከሚገባው በላይ ማሰቃየት፣ ቶርች ማድረግ፣ መግደል ለአባላቱና በየአካባቢው ለተዋቀረው ገዳይ ዕዝ ሙሉ መብት ተሰጥቶ እየተገበረ ይገኛል።

ዛሬ ሕዝባችንና ልጆቹ በወያኔ ገዳይ አዋጅ እየታነቁ ነው። በችግርና በረሃብ የተቀጣው ሕዝባችን በወያኔ ጥይት እየተለቀመ ነው። ወያኔ በየሚድያው ተራ ቅጥፈቱንና ፕሮፓጋንዳውን እየነዛ ውስጥ ውስጡን በርካታዎችን እየለቀመ ይገኛል። በተለይ በአለፈው አንድ ዓመት በተደረገው ሕዝባዊ እንቅስቃሴ በየስብሰባው፣ ሰልፉ ዋና ተሳታፊ የነበሩትን ከየቪድዮው እየለቀመ በመመንጠር ላይ ይገኛል። የፌስ ቡክ ተሳታፊዎችንና ተቃዋሚዎችን እያሳደደ ነው። ወያኔ በሽብር ዕድሜውን ለማራዘም እየተራወጠ ነው። ቀጥተኛ ጦርነት በማወጅ በተለይ በጎንደር አማራ ተወላጆችና በኦሮሞ ወገኖቻችን ላይ ጭፍጨፋ እያካሄደ ይገኛል። ወያኔ/ኢህአዴግ የባህሪውን እየተገበረ ይገኛል።

ህወሀት/ኢሕአዴግ አፋኝ የአስቸኳይ ጊዜ አዋጁን ተገን በማድረግ "ሁከት በመፍጠር፣ ሁከት በማነሳሳት፣ ሽብር በመንዛትና አለመረጋጋት በመፍጠር ወዘተ" በሚል ተራ ሰበብና አምባገነናዊ ጨካኝ ባህሪው በየቦታው በአቋቋማቸው ማጎሪያዎች፦ በአዋሽ ማዕከል፣ በጦላይ ማዕከል፣ በዝዋይ አላጌ ማዕከል፣ በዲላና ይርጋለም ማዕከል፣ በባህር ዳር ማዕከል፣ በአዲስ አበባ ማዕከል በ50 ሺህዎች የሚቆጠሩ ወገኖችን በማሰር እያሰቃየ ይገኛል። አሁንም እስሩና አፈናው በየቦታው በሠፊው ቀጥሏል።

ወያኔ/ኢሕአዴግ ከእንግዲህ በማንኛውም መልኩ ኢትዮጵያንና ሕዝቧን ጭምብል በለበሰ ዴሞክራሲው ሊያስተዳድር ተስኖታል። ሁሉም ነገር ጉም መጨበጥ ሆኖበታል። እንደልቡ እያጭበረበረ መዝረፍ የተሳነው ወያኔ ሀገርና ሕዝብ ማጥፋት እቅዱ ላይ ትኩረት ሰጥቶታል። ዳግማዊ ዮዲት ጉዲት ዘመን፣ ዳግማዊ ግራኝ አህመድ ዘመን በወያኔ እየተካሄደ ነው። ኢትዮጵያን ለመበታተንና ለማጥፋት አዋጁ ታውጇል። የኢትዮጵያ ሕዝብ ይህንን ዘመነ ጥፋት ከምንግዜውም በተለየ መልኩ አንድነቱን አጠንክሮ የመመከት ብቻ ሳይሆን በድል የመወጣት የታሪክ ኃላፊነት ተደቅኖበታል።

ሀገር ልጆቿን አድኑኝ እያለች ነው። ለጣልያን ወረራ ያልተበገረች ኢትዮጵያ ለአንድነቷ የሀገር ያለህ! የሕዝብ ያለህ! እያለች ነው። ለአኝዋክ ደም፣ ለኦሮሞ ልጆች ደም፣ ለአማራ ልጆች ደም፣ ለልጆቿ ደም ዕምባዋን ወደላይ እየረጨች ነው። ኢትዮጵያ ለልጆቿ እያለቀሰች ነው። የሀገርና የሕዝብ ፍቅር ከቶም የሌለው የወንበዴ ዘመን የመጨረሻውን በትር ሀገር ላይ እያሳረፈ ነው። ሕዝብና ልጆቹ በየደቂቃው ሕይወታቸውን ሲገብሩ የትግሉ አጋር የፖለቲካ ድርጅቶች አንድነታቸውን ሊያጠናክሩ ሲገባቸው ሲያላሉ፣ የዘር ፖለቲካ የፈጠረውን አጣብቂኝ ከማለዘብ ሲያጋግሉ፣ ከኢትዮጵያ እንገንጠል ባዮች "ኢትዮጵያን መበተን አለብን" ሲሉ፣ ዛሬም የፖለቲካ ተራ ቁማር ሲቆመር ማየት ወያኔ ወደቀ ወያኔ ተተካ እንዳይሆን ያሰጋል።

ኢትዮጵያ እንደ ሀገር አንድነቷንና ሉዓላዊነቷን አስጠብቃ ለሁሉም ልጆቿ ትሆን ዘንድ በቅድሚያ ኢትዮጵያዊነት ብሔራዊ ስሜት መጎልበት ይኖርበታል። በዘረኝነት ክልል ሀገር እንደማትገነባ ወያኔ አሳይቶናል። ከወያኔ የዘረኝነትን አባዜ ለመውረስ መንደርደር ጊዜው የዘረኝነት ነውና እሱን ተጠቅሞ ለሥልጣን መሮጥ ሊያስከትል የሚገባውን አደጋ አስቀድሞ ማጤን ተገቢ ነው።

የኢትዮጵያ አንድነት ስንል "የብሔር ብሔረሰቦች መብት እስከ መገንጠል" መፈክር "የብሔር ብሔረሰቦች መብት በኢትዮጵያ አንድነት" ማለታችን ነው። የኢትዮጵያ አንድነት ስንል የዘር አከላለል የአንድ ሀገር ልጆችን ይለያያል ባይ ነን። አንድ ሀገር! አንድ ሕዝብ! ስንል ኢትዮጵያ ታሪካዊ መለያዋን፣ የጀግኖች መኩሪያ፣ የአንድነት ዓርማዋ አረንጓዴ ቢጫ ቀይ ሰንደቅ ዓላማዋ ከተራራው ጫፍ በአራቱም ማዕዘን ይድመቅ ማለታችን ነው። ወያኔ/ኢሕአዴግ ለ25 ዓመት የረጨውን የዘር ፖለቲካ በማራገብ ስይሆን ማብቃት እንዳለበት ድፍረቱ ሲኖረን ሀገርንም ሕዝብንም ከአደጋ ልንታደግ እንደምንችል «አንድ ሀገር! አንድ ሕዝብ! ኢትዮጵያችን ሕዝባዊ ንቅናቄ» ጽኑ እምነታችን መሆኑን እየደጋገምን መግለጽ እንወዳለን።

በተለያየ ወቅት ሊከፋፍላትና አንድነቷን ሊያናጉ የመጡባትን የውጭ ወራሪ ኃይሎች መክታ ለትውልድ የተተላለፈች ኢትዮጵያ የወያኔ 25 ዓመት የዘር ፖለቲካ መርዝ የፖለቲካ ድርጅቶችን እንጂ የኢትዮጵያን ሕዝብ እንዳላናጋው በተለያዩ ጊዜ መልሱን ሰጥቶናል።

በ1997 ዓ.ም. የምርጫ ትርይት ለ14 ዓመት የተተከለውን ዘረኝነት በጥሶ የኢትዮጵያ ሕዝብ ዘር፣ ክልልና ሃይማኖት ሳይለይ በአንድነት ድምጹን ያሰማበት ዘመን የሀገር ፍቅሩንና የአንድ እናት ልጆች መሆናቸውን ያስመሰከሩበት ትርዕይት ነበር።

በቅርቡ በየአካባቢው በተደረገው ሕዝባዊ እንቅስቃሴ የኦሮሞ ልጆች ለአማራው መጮሃቸው፣ የአማራ ልጆች "ደማቸው ደማችን" ብለው ለኦሮሞ ልጆች መደብደባቸው፣ ጋምቤላዎች እናታችን ብለው ለኢትዮጵያ ከመተልተላቸው ባሻገር በየሰልፉና በየተቃውሞው መድረክ ስለ ኢትዮጵያ አንድነትና ስለ ኢትዮጵያዊነታቸው ሲጮሁ፣ የመብት ያለህ ሲሉ፣ "የሻቢያ ተላላኪ ወያኔ" ሲሉ ካስደመጧቸው ጩኸቶችና መፈክሮች ትምህርት መቅሰም ካልቻልን ምኑን ሀገር ለማዳን ተነሳን?

ዛሬ ኢትዮጵያ ሀገራችን በህወሀት/ኢሕአዴግ የገጠማት የመበታተን አደጋ በወያኔ ተቃዋሚ ስም የሌሎችም "እንበታተናታለን" ዛቻ ትግሉ ጥንቃቄን የሚጠይቅ መሆኑን እንድንገነዘብ ያደርገናል። ኢትዮጵያንና ህዝቧን ከመበተን አንፃር በአንድ በኩል ወያኔ/ህወሀት በሌላ በኩል ተቃዋሚ ዘረኞችና በታኞችን ካልታገልን "ኢትዮጵያ ለዘለዓለም ትኑር!" መፈክራችን በወረቀት እንዳይቀር ልንሰጋ ይገባናል። ሀገራችን አጥፊዋ በዝቶና ተበራክቶ ይታያል። የወያኔን በታኝ ሕገ መንግስት ተቀብለንና አሻሽለን እንንዝ ባይ አሳፋሪ ፖለቲከኛ ከሀገርና ሕዝብ አንድነት አንጻር ጎጂ እንጂ ጠቃሚታው የሳሳ ነው። ወያኔ ይውደምና የወያኔን ሕገ መንግሥት እንጠግነው እጅግ የሚቃረኑ አባባሎች መሆናቸውን ልንገነዘብ ይገባል። «አንድ ሀገር! አንድ ሕዝብ! ኢትዮጵያችን ሕዝባዊ ንቅናቄ» የኢትዮጵያንና የሕዝባችንን አንድነት ካስቀደምን ዘንዳ ወያኔም ሕገ መንግስቱም ወደ መቃብር እንላለን። አዎ! ***<u>የወያኔን ሕገ መንግስት ለማውደም የተዘጋጀ ትግል ነው ሥር ነቀል ለውጥ አስመዝግቦ የኢትዮጵያን የግዛት አንድነት አስጠብቆ ዴሞክራሲያዊት ኢትዮጵያን የሚገነባው</u>*** ስንል ብዕራችንን እናደምቃለን፣ ድምጻችንን እናሰማለን።

ኢትዮጵያ ለዘለዓለም ትኑር!

እግዚአብሔር ኢትዮጵያን ይባርክ!

"አንድ ሀገር! አንድ ሕዝብ! ኢትዮጵያችን ሕዝባዊ ንቅናቄ"

ህዳር 03 ቀን 2009 ዓ.ም. (November 12, 2016)

**<u>ማሳሰቢያ ፡</u>**

- ውድ ወገኖቻችን ይህንን «አንድ ሀገር! አንድ ሕዝብ! ኢትዮጵያችን ሕዝባዊ ንቅናቄ» «***ኢትዮጵያችን***» ዕትም በተለይ በሀገር ቤት ኮምፒዩተር የማግኘት ዕድል ለሌላቸው በማባዛት ታሰራጩት ዘንድ ቀና ትብብራችሁን በትህትና እንጠይቃለን።
- «አንድ ሀገር! አንድ ሕዝብ! ኢትዮጵያችን ሕዝባዊ ንቅናቄ» በቅርቡ መስከረም 8 ቀን 2009 ዓ.ም. እራሱን ይፋ ያደረገ ሕዝባዊ ድርጅት ሲሆን የንቅናቄውን ማንፌስቶና ፕሮግራም www.ethiopiachen.org ከሚለው ድረ ገጻችን ማግኘት ትችላላችሁ።

ኢሜል ፡ ethiopiachen2009@gmail.com
info@ethiopiachen.org
ድረ ገጽ ፡ www.ethiopiachen.org
www.ethiopiachen.com